# የአባላዘር ተላላፊ በሽታዎች እውነት ነገሮች

Genital Warts/HPV - Amh

## የብልት ኪንታሮት/ኤች-ፒ-ቪ
## (በሰው ፓፒሎማ ቫይረስ የሚነሳ-ኤች-ፒ-ቪ)

### የበሽታው ምልክቶች

የብልት ኪንታሮት የሚተላለፈው፣

- ቫይረሱ ከነኩ ከ 1 እስከ 6 ወሮች በኋላ
- በብልት ወይም ፊንጢጣ የሚወጣ ለስላሳ እብጠት
- በብልት አጠገብ ማቃጠልና ማሳከክ
- ኪንታሮት በሴት ብልትና ፊንጢጣ ሊደበቅ ይችላል
- ኪንታሮት አለሕክምና አይሄድም
- ኪንታሮት ሊሄድ ይችላል፣ ኤች-ፒ-ቪ ጀርም ግን ለብዙ ግዜ ይቆያል

### መተላለፍ

የብልት ኪንታሮት የሚጋባው፣

- በሴት ብልት ግብረስጋ ግንኙነት
- በአፍ ግብረስጋ ግንኙነት
- በፊንጢጣ ግብረስጋ ግንኙነት
- ኪንታሮት ከያዘው ጋር ግንኙነት
- ከታመመች እናት ወደ አዲስ የተወለደ ሕጻን
- የኪንታሮት ኤች-ፒ-ቪ በሽታ ባይታይም ከታመመ ሰው ጋር አለ ኮንዶም (ላስቲክ) ከተገናኑ በሽታው ይጋባል

### ጣጣውና የሚያስከትለው ችግር

የብልት ኪንታሮት ሳይታከም ከቀረ፣

- አዲስ ወደሚወለደው ሕጻን በመተላለፍ የጉሮሮ ኪንታሮት ሊፈጥር ይችላል
- ወደ ሌሎች የግብረስጋ ተካፋዮች ይጋባል

አንዳንድ ቫይረሶች እስጊ የማህጸንና የብልት ካንሰር ሊያስከትሉ ሲችሉ አይታዩም። ስለዚህ፣ ግብረስጋ የሚያደርጉ ሴቶች በያመቱ የፓፕስሚር ምርመራ ማድረግ አለባቸው።

ሃኪሞች ከካንሰር የተነሱትስ ንቃዮች ለማግኘት ልዩ ምርመራ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

### መከላከል

የብልት ኪንታሮት እንዳይዛመት የሚረዱ አስተያየቶች፣

- የብልት ኪንታሮትና ኤች-ፒ-ቪ ቫይረስ አብዛኛው ግዜ የኮንዶም መከላከያ በተደረገላቸው አካባቢ ነው የሚወጡት፣ መከላከያ ባልተደረገላቸው ቦታዎችም ሊወጡ ይችላሉ የላተክስ ኮንዶም የኤች-ፒ-ቪ በሽታን ሊከላከሉ የሚችሉት፣ የበሽታው ቦታ በኮንዶም ከተሸፈነ ብቻ ነው። በተጨማሪም ኮንዶም መጠቀም በኤች-ፒ-ቪ ቫይረስ የተነሳ የሚመጡት እንደ የማህጸን ካንሰር በሽታዎችስ ይከላከላል።
- የሴት ብልትና የፊስጢጣ ግብረስጋ ሲያደርጉ፣ ሁሉግዜ በኮንዶም ያድርጉ
- የወንድ ብልትና አፍ ግብረስጋ ሲያደርጉ የላቴክስ ኮንዶም ይጠቀሙ
- የሴት ብልትና አፍ ግብረስጋ ሲያደጉ ኮንዶሙን በሁለት በመክፈል መከላከያ ያድርጉ
- የግብረስጋ ተካፋዮችዎ ይቀንሱ
- የብልት ኪንታሮት ካለዎት ሃኪም ወይም በሌላ የህክምና አገልግሎት ይመርመሩ

### የብልት ኪንታሮት/ኤች-ፒ-ቪ ህክምና

- ኪንታሮትን ለማከም ይቻላል፣ለማዳን አይቻልም
- ሃኪም ያስፈልገዋል
- የሌላ ዓይነት ኪንታሮት የፋርማሲ ህክምና ከተጠቀሙ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል
- የሚታይ ኪንታሮት ካንሰር አያመጣም

**ለተጨማሪ ማብራርያ በሚከተለው ይጠይቁ፣**

Infectious Disease Epidemiology, Prevention and Control Division
STD and HIV Section
Minnesota Department of Health
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-5414

Minnesota Family Planning and STD Hotline
1-800-783-2287 **ድምጽ** /TTY

CDC National STD and AIDS Hotlines
1-800-227-8922; 1-800-243-7889 TTY